# አጠቃላይ ብክለት / Total Depravity

እነዚህ 5 Points ነገረ ድነትን የሚዳስሱ ናቸው ። ነገረ ድነት ደግሞ እጅግ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው ። ምክንያቱም አምላክ ሰው ሆኖ ስለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል የተሰቃየበት እና የሞተበት ጉዳይ ነው ። ይህ ብቻ ሳይሆን ለብዙ የኃይማኖቶች የመለያየት ምክንያታቸው ነገረ ድነት ነው ። ይህ ልዩ ነት የጀመረው በእኛ ዘመን ሳይሆን አስቀድሞም የነበረ ልዩነት ነው ። ስለዚህ ከመጀመሪያው ጀምሮ ያሉትን ልዩነቶች እንመልከት ።

በአራተኛው መቶ ክፍለዘመን የነበረው የአስተምህሮ ልዩነት እንደመነሻ አድርገን ብንመለከት ጥሩ ነው ብዬ አሰባለሁ ። ይህም በፔላጊየሰ እና በአውግስጢኖስ መካከል ያለው የአስተምህሮ ልዩነት ነው ። ፔላጊየሰ ለድነት የሰው ግብረ ገባዊ ሀላፊነት እንደሚያስፈልግ ይከራከር ነበር ። መዳን ከሰዎች የሚመነጭ በበጎ ስራዎችም ሊገዛ እንደሚችልም አስተምሯል ። ይህ ሰው ከጅምሩ በሂደትም እንዲሁም እስከመጨረሻ የእግዚአብሔር አጋዥ ፀጋ አያስፈልግም ይል ነበር። ደግሞም ሰው የሚድንበት መንገዱ እና አስፈላጊው ነገር ሁሉ በሰው ውስጥ ነው ያለው ይለናል ። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው እራሱን ማዳን እንደሚችል ያስተምር ነበር ።

ከእዚህ በተቃራኒው ደግሞ አልጄሪያዊው ቅዱስ አውግስጢኖስ ፔላጊየሰን በመቃወም ፅሁፍን ፃፈ። ሰው በውርሰ ኃጢአቱ ምክንያት ተበክሏል ደግሞም እራሱን ካወቀ በኋላ በፈቃዱ ኃጢአትን ያደርጋል ብሎ አስተማረ ። ከእዚህም የተነሳ ሰዎች ወደእግዚአብሔር መቅረብ እንዲችሉ ከእነርሱ ውጪ የሆነ extra የሆነ ኃይል ያስፈልገናል ብሎ ይከራከር ነበር ። በ 418 ላይ የተደረገው የካርቴጅ ጉባኤ የኦግስጢኖስን የፀጋ አስተምህሮ ሙሉ በሙሉ በማፅደቅ እና የፔላጊየሰን አስተምህሮ የምንፍቅና በማለት አውግዞታል ።

ከእዚያም በኤራስመስ እና በሉተር ይህ አይነት የአስተምህሮ ልዩነት ቀጥሏል ። በ1524 ኤራስመስ on the freedom of the will የሚልን መፅሐፍ ሲፅፍ ሉተር ደግሞ በአፀፋው በ1525 ደግሞ The bondage of the will የሚልን መፅሐፍ ፅፏል ። ኤራስመስ ሰው እግዚአብሔርን የመፈለግ ነፃነት አለው ሲል - ሉተር ደግሞ ሰው በኃጢአት ምክንያት እግዚአብሔርን የሚፈልግበት እና የሚገዛበትን ነፃነቱን አጥቷል ይለናል ።

ከእዚያም በመቀጠል ይህ አይነቱ የአስተምህሮ ልዩነት በጆን ካልቪን እና በጃኮብ አርሚኒየሰ መካከል በደንብ ዳብሮ የአስተምሮ ቅርፅ ይዞ መጣ ። ይህ ጃኮብ አርሚኒየሰ ከጆን ካልቪን በኋላ የመጣ ሰው ሲሆን ከካልቪን ጋር ፊት ለፊትም ተገናኝተው አያውቁም ። ነገርግን ከካልቪን ተማሪ ከቲዎዶር ቤዛ ጋር ግኑኝነት የነበረው እና የእርሱም ተማሪ የነበረ ነው ። ነገርግን በትምህርቱ እንዳልተሰማማና ጆን ካልቪን በእድሜው ካስተማራቸው ትምህርቶች በአምስቱ ላይ ተቃውሞ አዘጋጀ ። ከእዚያም የጃኮብ አርመኒየሰ ተከታዮች በአምስቱ ነጥቦች ላይ የተቃውሞ ሰነዶችን አስቀመጡ ። ከእዚያም በ1610 የዶርት ሲኖዶስ እነዚህን አመለካከቶች ውድቅ በማድረግ የተሃድሶን ትምህርት አፅድቆ የአርመንን ትምህርት ተቃርኖ መግለጫ አውጥቷል ።

በዶርት ሲኖዶስ በተፈጠረው መግለጫ መሰረት በአንዱ በኩል የያዕቆብ አርመን ትምህርት የሚከተሉ አርመናውያን (Remonstrants) በመባል ሲጠሩ - በሌላ በኩል ደግሞ የተሐድሶውን የጆን ካልቪን ትምህርት የያዙ (Counter Remonstrants) በመባል ይታወቃሉ ።

የአርመኒያን ትምህርት በጥንቃቄ ካየነው በተግባር Synergism ነው ። ሲነርጂዝም ማለት ፦ “አብሮ መስራት” የሚል ፍቺ ካለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መዳንን አብሮ ይሰራል የሚለው አመለካከት ነው ። ስለዚህ እነዚህን አምስቱ ነጥቦች አለመቀበላቸው ከ 5 solas ጋር ቀጥተኛ ግጭት አላቸው ማለት እንችላለን ። አንድ ሰው አምስቱ ብቻዎችን እቀበላለሁ ብሎ TULIPን የማይቀበል ከሆነ በተዘዋዋሪ አምስቱ solasን እየተቀበለ አይደለም ማለት ነው ። ለምሳሌ አንድ ሰው የቅዱሳን ፅናትን የማይቀበል ከሆነ ማለትም ድነቱን በሰራው የሚያጣ ከሆነ እና ድነቱን በሰራው የሚያስቀጥል ከሆነ በፀጋ ብቻን እና በእምነት ብቻን በቀጥታ ተቃውሞታል ማለት ነው ።

ስለዚህ ድነት የእግዚአብሔር ስራ ብቻ ነው የሚለው የተሐድሷዊያኑ ትምህርት መፅሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ግልጽ ነው ። ድነት የእግዚአብሔር ስራ ብቻ ነው የሚለው ሞነርጂዝም (Monergism) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ። ትርጉሙም ፦ “ብቻውን መሥራት” ከሚል ከተዋሃደ የግሪክ ቃል የመጣ ነው ። እግዚአብሔር ብቻውን ነው መዳናችንን የሰራው የሚል አመለካከት ነው። ይህ አመለካከት “የጸጋ አስተምህሮዎች” ተብሎ ከሚጠራው ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው ።

= ጆን ካልቪን በፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ ውስጥ ትልቅ ሚና ያለው እና ዛሬ በሥነ መለኮት ፣ በትምህርት እና በፖለቲካው ላይ ሰፊ ተጽዕኖ ያሳደረ ፈረንሳዊ የሃይማኖት ምሑር ነበር።

– የእንግሊካን ደራሲ ጄ.አይ ፓከር ስለ ካልቪን እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “ሌላ የሃይማኖት ምሑር በዓለም ታሪክ ውስጥ ይህን ያህል ሚና የተጫወተ ስለመኖሩ አጠራጣሪ ነው” ።

– ቻርለስ ስፑርጅን እንዲህ አለ፣ “በእድሜ በገፋሁ ቁጥር የጆን ካልቪን የሥነ-መለኮት ሥርዓት ወደ ፍጽምና በጣም የቀረበ ይመስላል” ።

– አሜሪካዊው የታሪክ ምሁር የሆኑት ጆን ፊስኬ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦ “የሰው ልጅ ለካልቪን ያለውን ዕዳ ከመጠን በላይ ማለፍ ከባድ ነው ። ይህ የተሐድሶ እንቅስቃሴ በእግዚአብሔር እርዳታ ዛሬ ወደእኛ ዘመን ተሻግሮ ብዙ ሰዎችን የዚህው የተሐድሶ አካል እያደረገ ይገኛል ። ከአምስቱ ነጥብቦች በቅድሚያ የተቀመጠውን total depravityን እንመልከት ።

## <u>ሁለንተናዊ ብክለት</u>

ሁለንተናዊ ብክለት ማለት ምን ማለት ነው ? ይህንን በሁለት መንገድ ለመመልከት እንሞክር ።

1ኛ, ግለሰባዊ ሁኔታን የሚመለከት ነው ። አንድ ግለሰብ ሁለንተናው በኃጢአት ተበክሏል ማለት ምን ማለት ነው ? ኃጢአት የሰውየውን እያንዳንዱን ክፍል ማለትም አዕምሮውን ፣ ፈቃዱን ፣ ስሜቱን እና ስጋውን አበላሽቶታል ማለት ነው ። በሌላ አገላለጽ ኃጢአት ማንነታችንን እና የምናደርገውን ነገር ጨምሮ በሁሉም የሰውነታችን ክፍሎች ላይ ተፅዕኖ ያደርጋል ማለት ነው ።

2ኛ, ማህበራዊ ሁኔታን የሚመለከት ነው ። ማህበራዊ የኃጢአት ብክለት ማለት ምን ማለት ነው ? እያንዳንዱ ሰው መበከሉን የሚያመለክት ነው ። ኪዳን ያለውም ኪዳን የሌለውም ህዝብ ከኃጢአት ብክለት ነፃ አይደለም ። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 3፡9-18 ያለውን የሰውን አጠቃላይ ርኩሰት ጠቅለል አድርጎ ሲገልፅ እንዲህ በማለት ነው ፦ “አይሁድም ግሪኮችም ሁሉም በኃጢአት ሥር ናቸው” በማለት ነው። በቀላል አነጋገር፣ ይህ ማለት ሰው በኃጢአት ቁጥጥር ሥር ነው ወይም (በተፈጥሯዊው የኃጢአት ዝንባሌ) ቁጥጥር ሥር ነው ማለት ነው።

## ይህንን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰፋት ትኩረት ተሰጥቶት እንመለከታለን ።

## ብሉይ ኪዳን

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ የተፃፉትን ሁሉንም የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል በእዚኛ ትምህርት ማብራራት አይቻልም ። ነገርግን  የተወሰኑ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባትን በማንሳት መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት መሆኑን ለማሳየት እሞክራለሁ ።

ይህንን ከአዳም ውቀት ጊዜ ጀምሮ ያለውን መመልከት እንችላለን ። አዳም ከውድቀቱ በፊት የነበረበትን ሁኔታ ስንመለከት ከእግዚአብሔር ጋር ጥሩ ግኑኝነት ነበረው ። በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብ ይልቅ ከእግዚአብሔር እንደሸሸ እናውቃለን ። እግዚአብሔር አዳምን ወዴት ነህ? ብሎ ሲጠይቀው አዳም የሰጠው ምላሽ ፈራሁም ተሸሸኩም ነበር ያለው ።

ይህ ችግር አዳም ጋር ብቻ አላበቃም ከእዚያም በኋላ የነበሩት ሰዎች ጋር ይህንን መመልከት እንችላለን ። ለምሳሌ ፦ “እግዚአብሔር (ያህዌ) አምላክ የሰው ዐመፅ በምድር ላይ የበዛና የልቡም ሐሳብ ዘወትር ወደ ክፋት ብቻ ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ።” — ዘፍጥረት 6፥5 (አዲሱ መ.ት) ።

በእዚህ ክፍል በዋናነት ሁለት ነገር መመልከት እንችላለን ። 1, የሰው ልጅ ዝንባሌ ለአመፅ መሆኑን ።

2, ሌላኛው ከአመፅ ውጪ ለምንም ነገር ቦታ የሌለው መሆኑን መመልከት እንችላለን ። ይህንንም ብቻ በሚለው ቃል መረዳት እንችላለን ።

– እንዲሁ በኤርምያስ 17:9 “የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነው፤ ፈውሰም የለውም፤ ማንስ ሊረዳው ይችላል?” — ኤርምያስ 17፥9 (አዲሱ መ.ት) ።

– በመዝሙር መፅሐፍም ላይ ይህንን አይነት አገላለጽ ይጠቀማል ። መዝሙር 14  [2] የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ። [3] ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ፤ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም፤ አንድም ስንኳ የለም።

## አዲስ ኪዳን

ደግሞ ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ የዮሐንስ 3 ላይ መመልከት እንችላለን ። “ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለ ነበረ፣ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፤” — ዮሐንስ 3፥19 (አዲሱ መ.ት) ። በጣም የሚገርመው ብርሃን ወደ አለም መጥቶ እንኳን ሰዎች ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ነው የወደዱትን ። ይህ የሰው ልጅ ምን ያህል ብርሃንን የሚጠላ እንደሆን መመልከት እንችላለን ። እግዚአብሔር ብርሀን ነው ። ኃጥያት እና ሀጥያተኛ በጨለማ ይመሰላል ። ጨለማ ሁል ጊዜ ከብርሃን ይሸሻል። መሸሽ ብቻም አይደለም ብርሃንን ይቃወማል ።

– የሮሜ መፅሐፍ ከምዕራፍ 1-3 ድረስ በዋናነት ይህንን በሰፋት ያሳያል ። – በምዕራፍ 1 የአህዛበን ብክለት በዝርዝር ይነግረናል ። 1 ,እግዚአብሔር የለም አሉ ። ሮሜ 1 (አዲሱ መ.ት) [19] ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው ለእነርሱ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእነርሱ ግልጽ አድርጎታል። [20] ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል፤ ስለዚህ ሰዎች ማመካኛ የላቸውም።

2, እግዚአብሔርን ቢያውቁም እንኳን እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን አላከበሩትም።

3, እግዚአብሔርን በጣዖት መሰለው ለውጡ ። እግዚአብሔርን በጣኦት መሰለው የለወጡበትን መንገድ ሲያብራው እንዲህ ባለ መንገድ ነው ። “የዘላለም አምላክን ክብር ምዉት በሆነው ሰው፣ በወፎች፣ በእንስሳትና በምድር ላይ በሚሳቡ ፍጥረት መልክ መሰለው ለወጡ።” — ሮሜ 1፥23 (አዲሱ መ.ት) ።

4, በስተመጨረሻ በሃሳባቸው ከንቱነት እግዚአብሔርን ማወቅ አይጠቅምም አሉ ።

– በምዕራፍ 2 የአይሁዳውያን ብክለት በዝርዝር ይነግረናል ።

እግዚአብሔር ህግ ቢሰጣቸውም በኑሮአቸው ህግ እንደሌላቸው ሰዎች ሆኑ። አትስረቅ እያሉ የሚሰርቁ ።

አታመንዝር እያሉ የሚያመነዝሩ ። ህጉን የሚሰሙ እንጂ የማይጠብቁ ናቸው ።

በምዕራፍ 3 ደግሞ በአጠቃላይ ከአዳም ጀምሮ ክርስቶስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ያለውን የሰዎችን እርኩሰት ጠቅለል አድርጎ ይገልጻል ።

– “ለኀጢአት የተገዛ አእምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፤ መገዛትም አይችልም።” ሮሜ 8፥7

**ከአረመኒያኖች የሚነሳ ጥያቄ**

እነዚህን እና የመሳሰሉትን መፅሐፍ ቅዱስ ምንባባትን ለአርመኒያኖች እንደማስረጃ አድርገን ስናቀርብላቸው እንርሱ መልሰው በመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውሰጥ እኛም የምናቃቸው ሰዎች መልካም ተጋራቶችን ሲያደርጉ እናያቸው የለ እንዴ ? ታድያ እንዲህ ከሆነ የሰው ልጅ ሁለንተናው ተበክሏል እንዴት እንላለን ይለናል ።

ይህ ጥያቄአቸው እኛ reformedኦች እያልን ቻለነውን እንዳልተረዱ እንደሆነ ያመለክታል ። እኛ እያልን ያለነው በታሪክ ውሰጥ መልካም ሰዎች አልተገኙም ደግሞም በታሪክ ውሰጥ መልካም ሰራ አልተሰራም እያልን አይደለም ። ሰው በተፈጥሮው በራሱ ችሎታ መልካም ነገር ሊያደርግ አይችልም ነው እያልን ያለነው ። ነገርግን ሰው በእግዚአብሔር ፀጋ ታግዞ መልካም ነገሮችን ሊያደርግ ይችላል ። ይህ መልካም ነገር በሚያምኑም በማያምኑም ሰዎች ሊደረግ ይችላል ። በማያምኑ ሰዎች መልካም ነገሮች ሲደረግ Common grace እንላለን ። በሚያምኑ ሰዎች መልካም ነገሮች ሲደረግ Spatial Grace እንላለን ። በማያምኑ ሰዎች የሚደረጉ መልካም ነገሮች ለድነት አያበቁም ። ነገርግን እግዚአብሔር በሞግቦቱ ምድርን ለማስቀጠል የሚጠቀመው መልካምነት ነው ።

## Unconditional Election

ይህንን topic አብዛኛው ሰዎ በመዝሙር የሚቀበለውና የሚባረክበት ሲሆን ፣ ዶክትሪን ሲሆን ግን የሚቃወመው topic ነው ። ሳልወድህ የወደድከኝ ፣ ሳልመርጥህ የመረጥከኝ የሚለውን የተሰፋዬ ጫላን መዝሙር እየዘመረ ፣ የመረጥከኝ ተባረክልኝ የሚለውን የአገኘው ይደጉን መዝሙር እየዘመረ unconditional election ስትለው ይቃወምሀል ። ይህ ችግር የሚዘምሩትን መዝሙር በትክክል ካለመረዳት የሚያመነጭ ወይንም መዝሙሩን በጥልቀት ካለማሰብ የሚመጣ ነው ። በተቻለን መጠን የዘመርነውን እንወቅ ደግሞም የምናውቀውን እንዘምር ።

– አስቀድሞ መምረጥን ሰናስብ በቅድሚያ መነጋገር ያለብን ጉዳይ እግዚአብሔር ሰራውን ሲሰራ እንዴት ነው የሚሰራው ? የሚለውን ነው ። በዘፈቀደ ነው የሚሰራው ወይንስ በእቅድ ? የትኛውም እማኝ በአቦ ሰጥ ነው የሚሰራው የሚለኝ የለውም ። እግዚአብሔር ሲሰራ የሚሰራው ሁሉን በዕቅዱ መሰረት ነው ። ይህንን በኤፌሶን መፅሐፍ ላይ መመልከት እንችላለን ። "ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፤" — ኤፌሶን 1፥11 (አዲሱ መ.ት) ።

ከእዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ማንሳት ያለብን ጥያቄ እነዚህ የእግዚአብሔር እቅዶች ወደ መሆን የሚመጡት በሁኔታዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው ወይንስ በእግዚአብሔር ሉአላዊነት የሚለውን መመለስ አለብን ።

የመጀመርያው ፈፅሞ ሊሆን አይችልም ። ምክንያቱም እግዚአብሔር አቃጅ አምላክ ነው ብለን ከተሰማማን በተዘዋዋሪ ነገሮቹ በየት በኩል መሰመር መያዝ እንዳለባቸው ወሰኗል እያልን ነው ። ሰለዚህ ሊሆን የሚችለው ሁለተኛው ነው ። ይህም የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት በቀጥታ የሚመለከት ነው ። እግዚአብሔር ሉአላዊ ነው ሰንል አስያልን ያለነው ፦ ከእሱ ዕውቀት እና ከእርሱ ቁጥጥር ውጪ የሆነ አንዳች ነገር የለም ። ሁሉንም በሥልጣኑ ቃል ይቆጣጠራል። ከግዑዝ አካል እስከ ሰብዓዊ ፍጡር መላው አጽናፈ ዓለም ውሰጥ ያሉ ነገሮች ከእርሱ በታች ናቸው ማለታችን ነው ።

– "የምድር ሕዝቦች ሁሉ፣ እንደ ኢምንት ይቈጠራሉ፤ በሰማይ ኀይላት፣ በምድርም ሕዝቦች ላይ፣ የወደደውን ያደርጋል፤ እጁን መከልከል የሚችል የለም፤ 'ምን ታደርጋለህ?' ብሎ የሚጠይቀውም የለም።" ዳንኤል 4፥35 (አዲሱ መ.ት) ። እንዲሁም – ኢሳይያስ 46 ⁹ የጥንቱን፣ የቀደመውን ነገር አስታውሱ፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም፤ እኔ አምላክ ነኝ፤ እንደ እኔ ያለ የለም።¹⁰ የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤ 'ዐላማዬ የጸና ነው፤ ደስ የሚያሰኘኝንም ሁሉ አደርጋለሁ' እላለሁ።

– እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንደ ወደደው እንደ ፈቃዱ የሚያደርግ ከሆነ ይህ ነገር ድነትንም የሚያካትት ነው ? መልሱ አዎ ነው ። ለምሳሌ ፦ ኤፌሶን 1፡5 እንዲህ ይላል፦ "በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ_ወስነን ።" ኤፌሶን 1፥5 ።

በእዚህ በኤፌሶን መፅሐፍ 1፡3-14 ። የበረከት አይነቶችን ይዘረዝራል ። 1 መመረጥ በረከት ነው ። ከቁጥር ። 2, ልጅ መሆን በረከት ነው ። 3, ወራሽ መሆን በረከት ነው ። በእዚህ መፅሐፍ ጳውሎስ ምርጫን እንደበረከት ወሰዶት ለመባረክ ይጠቀማል ። ለእዚህ ነው የባረከን ይባረክ የሚለው ። ዛሬ ላይ የምርጫ ጉዳይ የክርክር ምክንያት መሆኑ ያሰገርመኛል ።

### መቼ ነው ምርጫው የተካሄደው ?

አለም ከመፈጠሩ በፊት ። ይህንን በቁጥር 3 ላይ አስቀምጦልናል ። አለም ከመፈጠሩ በፊት ይለናል ። የኢንጊሊዘኛው ቃል before the foundation of the world የግንባታን ሁኔታ የሚያነሳ ነው ። አንድን ሰራ ለመሰራት አስቀድሞ መሰረት ስለመጣል ነው የሚናገረው ። ከዚያም ቀድሞ የሚል ሀሳብ አለው ማለትም መሰረት ከመጣሉ አስቀድሞ ። ይህ የሰዎች ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ጠርጎ ሊያወጣ የሚችል አገላለጽ ነው ። ሰዎች እና እምነታቸው በሌለበት ሁኔታ የተጠናቀቀን የእግዚአብሔርን ሰራ የሚገልፅ ነው ።

### ለምንድነው የተመረጥነው ? ለአገልግሎት ወይንስ ለድነት ?

ምርጫው ግልፅ በሆነ ሁኔታ ሰለ ድነት ነው ። ይህንን ልጆቹ እንሆን ዘንድ መረጠን በሚለው መረዳት እንችላለን ። መቼስ ልጅ መሆን አገልጋይ መሆን ማለት አይደለም ። በተለይም በእዚህ በኤፌሶን መፅሐፍ ልጅነትን ከድነት

ጋር እያይዞ ነው የሚገልፅልን ። አስቀድሞ በምዕራፍ 2 ላይ የቁጣ ልጆች ይለንና በምዕራፍ 5:1:2 እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትመስሉ ሁኑ ይለናል ። በቁጥር ሁለት ደግሞ ክርስቶስ እንዴት ወደደን የሚለውን ይገልፅልናል ። በእነዚህ ምንባባት ልጅነት ከድነት ጋር የተገናኘ መሆኑንን መመልከት እንችላለን ።

ምርጫ ለድነት እንደሆነ በተሰሎንቄ መፅሐፍ እናገኛለን ። “በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፤ እኛ ግን ሁል ጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ይገባናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር እናንተን ከመጀመሪያ አንሥቶ በመንፈስ ተቀድሳችሁና በእውነትም አምናችሁ እንድትድኑ መርጦአችኋል።” — 2ኛ ተሰሎንቄ 2፥13 (አዲሱ መ.ት) ።

## ምርጫ ለዘላለም ህይወት ብቻ ነው ? ወይንስ ለዘለአለም ጥፋትም ነው ?

ሰዎች ለዘለዓለም ህይወት ተመርጠዋል ካልን በተመሳሳይ መንገድ ለዘለአለምም ሞት ተመርጠዋል ። መመረጥ እንዱ ያለአንዱ ትርጉም የለውም ። የሚተው ከሌለ መምረጥ ትርጉም የለውም ። ሁለቱም በአንዴ ነው የሚከሰቱት ። ሁለቱም ከዘለዓለም አንድነት ቀን አላቸው ። አንድ ወንድ አንድን ሴት ለትዳር ከመረጠ ያለመረጣቸው ብዙ ሴቶች አሉ ማለት ነው ። እዚህ ጋር negative inference fallacy አይሰራም ። ለምሳሌ ፦ እኔ ሐዋሳ ነኝ ማለት አዲስ አበባ አይደለሁም ማለት ነው ። መመረጥ በውስጡ አለመመረጥን ያቅፋል ።

ሰዎች ለፍርድ እንደተመደቡ መፅሐፍ ቅዱስ በግልጽ አስቀምጧል ። “ደግሞም፣ “ሰዎችን የሚያሰናክል፣ የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ።” የሚሰናከሉት ቃሉን ባለመታዘዛቸው ነው፤ የተመደቡት ለዚህ ነውና።” — 1ኛ ጴጥሮስ 2፥8 (አዲሱ መ.ት) ።

ያያዕቆብ ወንድም የሆነው ይሁዳ ስለነዝህ ሰዎች በመልእክቱ አሥፍሯል "ከረጅም ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንድ ሰዎች ሾልከው ወደ እናንተ ገብተዋልና፤ እነርሱ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው፣ የአምላካችንን ጸጋ በርኵሰት የሚለውጡና እርሱ ብቻ ልዑል ገዛችንና ጌታችን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው" ይሁ 1፥4። ስለእነዚህ ሰዎች ሲገልጽ "ከረጅም ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ" ብሏቸዋል። ይህም ረጅም ግዜ ተብሎ የተገለጸው ምን ይሆን? በሁለት መንገድ ትርጉም ተሰጥቶበታል ።

1, ለፍርድ ከፍጥረተ ዓለም አስቀድሞ የተወሰኑ "ምርጦች" ሲሆን ። 2, ወይንስ ከብሉይ ኪዳን ጊዜ ጀምሮ ሀሰተኞች ፍርድ እንደሚገባቸው እየገለፀ ነው የሚል ነው ። ሁለተኛው አገላለጽ ዕብራውያን 1 ላይ ይመስላል ። “እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በተለያየ ጊዜና በልዩ ልዩ መንገድ በነቢያት በኩል ለአባቶቻችን ተናገሮ፣”ዕብራውያን 1፥1 (አዲሱ መ.ት) ። የተሻለው የሰነ አፈታት መንገድ ለፍርድ እንደተወሰኑ ማመን ነው ። ብሉይ ኪዳን ላይ ሐሰተኛ አስተማሪዎች እንደሚነሱ ተናግሯል ? የሚል ጥያቄ ይነሳል ። መልሱ የለም ነው ። በእርግጥ የእግዚአብሔር እውነት ባለበት በተቃርኖ የሚነሱ ስህተቶች እና አሳቾች እንዳሉ እናውቃለን ። ነገርግን በብሉይ ኪዳን ይህንን አስመልክቶ Precisely የተነገረ ትንቢት የለም ። ጆን ጊል እንደሚለው በእዚህ ጉዳይ ላይ በብሉይ የተፃፈ አንድም ነገር አናገኝም ይላል ። ስለዚህም ፦ ይሄ የሚናገረው የሚጠፉ ሰዎች ከዘላለም በፊት የተወሰኑ መሆናቸውን ነው ይላል ጊል ።

ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ድንጋጌ ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ጥያቄዎች በቀላሉ መልስ ይሰጥበታል ። ሮሜ 9 (አዲሱ መ.ት) [19] ከእናንተ አንዱ፣ “ታዲያ እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር እስከ አሁን ለምን ይወቅሰናል? ምክንያቱም ፈቃዱን ሊቋቋም የሚችል ማን አለ?” ይለኝ ይሆናል። [20] ነገር ግን ለእግዚአብሔር መልስ የምትሰጥ አንተ ማን ነህ? “ሥራ ሠሪውን፣ ‘ለምን እንዲህ ሠራኸኝ?’ ይለዋልን?” [21] ሸክላ ሠሪ፣ ከሚሠራው ጭቃ፣ አንዳንዱን ሸክላ

ለክብር፣ ሌላውን ደግሞ ለተራ አገልግሎት የማድረግ መብት የለውምን? ይህንን የምርጫ አስተምህሮ አንዳንድ ሰዎች ከድነት ጋር የተገናኘ ሳይሆን ከአገልግሎት ጋር ነው የሚሉ ሰዎች አሉ ። መልሱን በደታች በመውረድ እናገኛለን ። ሮሜ 9 (አዲሱ መ.ት) [22] እግዚአብሔር ቍጣውን ለማሳየት፣ ኀይሉንም ለማሳወቅ ፈልጎ የቍጣው መግለጫ የሆኑትን፣ ለጥፋትም የተዘጋጁትን እጅግ ታግሦ ቢሆንሳ! [23] አስቀድሞ ለክብር ላዘጋጃቸው፣ የምሕረቱም መግለጫዎች ለሆኑት፣ የክብሩ ባለጠግነት እንዲታወቅ ይህን አድርጎ እንደሆነስ? [24] የጠራው ከአይሁድ ወገን ብቻ ሳይሆን ከአሕዛብ ወገን የሆነውን እኛን እንኳ ሳይቀር አይደለምን? [25] በሆሴዕ እንዲህ እንደሚል፤ "ሕዝቤ ያልሆኑትን፣ 'ሕዝቤ' ብዬ እጠራቸዋለሁ"፤ ያልተወደደችውንም 'የተወደደችው' ብዬ እጠራለሁ። [26] ደግሞም፣ " 'ሕዝቤ አይደላችሁም'፤ ተብሎ በተነገራቸው በዚያ ቦታ፣ 'የሕያው እግዚአብሔር ልጆች' ተብለው ይጠራሉ።"

– ሌላኛው የሚነሳው ጥያቄ ፦ እግዚአብሔር አስቀድሞ ሰዎችን ከመረጠ ወንጌል ለምን እንሰብካለን? ፣ የተመረጡ ሰዎች መዳናቸው አይቀርም ይላሉ ። ይህ የምርጫን አስተተምህሮ በትክክል ካለመረዳት የሚመጣ ጥያቄ ነው ። ኃይሉ ያለው በወንጌል መልእክት እና በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ላይ ያለ እንጂ በራሳችን ደካማ አቀራረብ ላይ እንዳልሆነ እናውቃለን ።

የምርም አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ምርጫ በትክክል ከተረዳ የወንጌል መልእክት እንዲሰፋፋ ኃይልን ያገኛል። ለምሳሌ፦ "ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እነርሱም ያገኙ ዘንድ፣ ለተመረጡት ስል ሁሉንም በመታገሥ እጸናለሁ።"( 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:10 ) ።

ስለ ምርጫ አስተምህሮ ትክክለኛ ግንዛቤ ወንጌላዊነትን ያበረታታል ለውጤቱም ዋስትና የሚሰጥ ነው። አንድ ሰው መመረጡን ወይም አለመመረጡን ለመረዳት መጣር ይህ የእኛ ጉዳይ አይደለም! ንስሃ ለሚገባ እና በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የመዳን ተስፋ ሁል ጊዜ አለ። እግዚአብሔር በጎቹን ወደ ራሱ ለመሳብ እንደሚጠቀምበት በማወቅ የወንጌል መልእክት ለሰዎች ሁሉ መሰበክ አለበት።

– ባይሆን ይህንን ጥያቄ መጠየቅ ያለብን እኛ ነን ። ምክንያቱም ፦ "ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፤ አድራጎቱም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን አይመጣም።" — ዮሐንስ 3፥20 (አዲሱ መ.ት) ።

ሁሉም ክፍ እንደሚያደርግ ተናገረ ፣ ከእዚህም ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ወደ ብርሃን አይመጣም ይለናል ። ታድያ እንርሱ ለምን ወንጌልን ይሰብካሉ ? ወይ ወንጌልን መሰበክ የለባቸውም ወይም ደግሞ በእግዚአብሔር ምርጫ ማመንና የሚድኑ ሰዎች እንዳሉ ተሰፋ በማድረግ ወንጌልን መሰበክ አለባቸው ።

## ውሰን ቤዝሆት (L –Limited atonement)

ከአምስቱ የካልቪኒዝም ነጥቦች፣ የተገደበ (ውሱን) ስርየት በጣም አከራካሪ ነው ። ይህ ትምህርት በዋነኛነት የሚያሳስበው እግዚአብሔር ክርስቶስን ወደ ዓለም በመስቀል ላይ እንዲሞት የላከበትን የመጀመሪያ ዓላማ ነው ። አላማውን በተመለከተ በዋናነት ሁለት አይነት ምልከታዎች አሉ ። 1ኛ ለሁሉም መዳን ይቻል ዘንድ ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት አሳልፎ ሰጠ የሚል ሲሆን – 2ኛ እግዚአብሔር ከዘላለም ጀምሮ የማዳን ዕቅዱ የመረጣቸውን ማዳን ነው የሚል ነው ።

የኃጢያት ክፍያው በመጀመሪያ ዲዛይኑ አስቀድሞ የተወሰነ ነበር ። የክርስቶስ የመስቀል ላይ የቤዝሆት ስራ ለተመረጡት እና ለሁሉ ያልሆነ ውሱን ነው ። ውሰን (የተገደበ) ሲባል እየተባለ ያለው ፦ በኃይሉ ሳይሆን በውጤቱ ነው ። የክርስቶስ ሞቱ ሁሉንም ማዳን ስለማይችል ሳይሆን አላማው ሁሉንም ማዳን ስላልሆነ ነው ።

በጣም የሚገርመው አርመኒያኖችም የክርስቶስን ሞት limete ያደርጉታል ።

ይህንንም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 እና በ1ኛ,ጴጥሮስ ምዕራፍ 1 መመልከት እንችላለን ። ምንም እንኳን ብዙ የመፅሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ቢኖሩም ። የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10 ላይ

1. የበጎች እረኛ አለ ። (ኢየሱስ)  2. ቅጥረኞች አሉ ። (ፈሪሳዊያን ናቸው)  3. በጎች አሉ ( በእግዚአብሔር የተመረጡ )።  4. በጎች ያልሆኑ አሉ (በእግዚአብሔር ያልተመረጡ)። 5, ሌባ የተባለው ( ሰይጣን ሊሆን ይችላል )

ታድያ እውነተኛው እረኛ (ኢየሱስ) ሲመጣ በጎቹን ከሌቦቹ ሊያድን ሲል ነፍሱን አሳልፎ የሰጠው ለማን ነው ? በዮሐንስ ዘገባ ለሁሉም ሳይሆን ለበጎቹ መሆኑን እንረዳለን “መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል፤” ዮሐንስ 10፥11 (አዲሱ መ.ት)።  እንግዲህ በዮሐንስ ወንጌል በጎች ያልሆኑ እንዳሉ ግልጽ ነው! በዚህም የክርስቶስ ሞት አላማ ግልጽ ሆኖ እናገኘዋለን ።

ሁለተኛው እንደማስረጃ መቅረብ የሚችለው 1 ጴጥሮስ 1:1-2 ላይ ያለውን ነው ። “የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፥ እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት በጳንጦስና በገላትያ በቀጰዶቅያም በእስያም በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች፤ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።”  — 1ኛ ጴጥሮስ 1፥1-2 ።

እግዚአብሔር የሚመርጥ ፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለመረጣቸው ደሙን የሚያፈስ ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚቀድስ ሆኖ ነው በዚህ ምንባብ የተገለጸው ። ይህ ከመቅደሱ ስረአት ጋር እንደሚገናኝ ነው ። በመቅደሱ ውስጥ የተመረጡ እቃዎች አሉ ፣ በተመረጡ እቃዎች ላይ ደም ይረጫል ፣ ከዚያም ለአገልግሎት ይለያሉ ። ይህ ከCovenant of Redemption ጋር የሚገናኝ ነገር አለው ።

John owen life by his death  በሚለው መፅሐፍ ላይ ቆንጆ ሙግት (Argument) አስቀምጧል ።

ከሚቀርቡት ሙግቶች መፅሐፍ ቅዱሳዊ የቱ ነው ?

1ኛ, ክርስቶስ ለሁሉም ሰው - ለተወሰኑ ኃጢአታቸው ሞተ

2ኛ, ክርስቶስ ለሁሉም ሰው - ለሁሉም ኃጢአታቸው ሞተ

3ኛ, ክርስቶስ ለተወሰኑ ሰዎች - ለሁሉም ኃጢአታቸው ሞተ

የመጀመሪያው ፈፅሞ አያስኬድም ። ምክንያቱም ክርስቶስ የኃጢአት እዳቸውን በከፊል ከልከፈለ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አንድም ፍጥረት አይኖርም ።

ሁለተኛውም ፈፅሞ አይሆንም። ክርስቶስ ለሁሉም ሰው ለሁሉም ኃጢአታቸው ዋጋ ከከፈለ አንድም ሰው ገሀነብ አይገባም ማለት ነው ። ምክንያቱም ወደ ገሀነብ ሊያስገባቸው የሚችለውን ሁሉ የኃጢአት ዋጋ ክርስቶስ ስለከፈለ።

ሶስተኛው ግን መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው ። ኢየሱስ የሞተው ለእግዚአብሔር ምርጦች (ለተወሰኑ ሰዎች) ነው ። እና ለሁሉም ኃጢአታቸው ።  ከዚህ የተነሳ ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰላቸው ሰዎች የለምንም እና ያለማንም ከልካይ ወደ እግዚአብሔር መንግሰት ይገባሉ ።

## ከውሰን ቤዝሆት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጥያቄዎች

"ሁሉ" የሚሉ እና አለም የሚሉ የመፅሐፍ ቅድስ ቃላት እንዴት ይታያሉ ?የሚሉ ናቸው ።

ከሚነሱ ጥያቄዎች መካከል አንዱን እንደምሳሌ ለመጥቀስ – 1ኛው  ዮሐ 1:29 ላይ ያለውን ነው ። "ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤" ዮሐንስ 1፥29 የሚለው ነው ። ዓለም የሚለው ቃል ሁል ጊዜ መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰናገኝ አንድ አይነት ትርጉም እንዳለው ማሰብ ስህተት  ይሆናል ። ዓለም የሚለው ቃል በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለያየ ትርጉምን አዝሎ እናገኛለን ።

ዓለም አንዳንድ ጊዜ ፦ይህ የሚታየውን አለም ማለትም ተራራ ፣ ሜዳ ፣ ድንበሩን የሚገልጽ ሲሆን ። ሌላ ጊዜ ክፋትን ለመገልፅ ያገለግላል ። እንዲሁም ሰዎችን ለመግለፅ ጥቅም ላይ ውሏል ። ሰዎችንም ሲገልፅ በጥንቃቄ መመልከት ያሰፈልገናል ምክንያቱም  እያንዳንዱን ሰው ላይወክል ስለሚችል ። ለምሳሌ ፦ "ከዚያም የአስቆሮቱ ያልሆነው ይሁዳ፣ "ጌታ ሆይ፣ ታዲያ፣ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ የምትገልጠው እንዴት ነው?" አለው።"  — ዮሐንስ 14፥22 (አዲሱ መ.ት) ።

ታዲያ የዮሐንሰን 1:29 ክፍል ሀሳብ ምን ይሁን? አለም ሲል ለእያንዳንዱ ሰው ፣ አንድም ሰው ሳይቀር እያለ ነው ? አይመሰልም ። ምክንያት ፦ ዓለም የሚለውን ቃል ትርጉም ለመረዳት የክፍሉን አውድ መረዳት ጠቃሚ ነው። ይህንን ያለበትን አውድ የምናገኘው መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን የንስሐ ጥምቀት እያጠመቀ ባለበት ሁኔታ ውሰጥ ነው ። የመጥምቁ ዮሐንስን አገልግሎት አራቱም ወንጌላት ዘግበውታል ። ምናልባትም ሰፋ አድርገን ለማየት ከሞከርን ዓለም የሚለውን ቃል ትርጉም እናገኛለን ። ለምሳሌ ማቲዎስ ላይ ያለው አቀማመጥ ከዮሐንስ ይልቅ ዓለም የሚለውን ቃል ለመተርጎም ብርሃንን ይሰጣል ።"'አብርሃም አባት አለን' በማለት ራሳችሁን አታታሉ፤ እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣ ይችላል እላችኋለሁና።" ማቴዎስ 3፥9 (አ. መ.ት) አብረሃም አባት አለን የሚሉት እሰራኤላውያን ናቸው ፣ እነዚህ ድንጋዮች የተባሉት ደግሞ አህዛብ ናቸው ። ማቲዎስ እያለ ያለው አሕዛም የእግዚአብሔር ልጆቹ ይሆናሉ የሚል መልዕክት እያስተላለፈ ነው ።

በአዱሱ ኪዳን ሰር ልጅነት ለአይሁድ ብቻ ሳይሁን ከአይሁድ ውጪ ላለው ዓለም ሁለ መሆኑን እየገለፀ ነው ። በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር በረከት በተለየ መልኩ ለእስራኤል ይሰጥ ነበር  በአዲሱ ኪዳን ዘመን ደግሞ ለህዝቦች ሁሉ ይሰጣል ። እንግዲህ መጥሙቁ ዮሐንሰ " የአለምን ኃጢአት የሚያሰወግድ የእግዚአብሔር በግ" ሲል የኢየሱስ ክርስቶስ በረከት የሚሰጠው ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለአህዛብም ጭምር መሆኑን ለመግለጥ ሊሆን እንደሚችል አመልካች ነው ።

### – ኢየሱሰ ለሁሉም ሰዎች ሞቷል የሚለው አሉታዊ( የሚያስከትሉት መፅሐፍ ቅዱሳዊ ተጣርሶዎች) ።

1, ግዚአብሔርን ኢፍትሐዊ ያደርገዋል ።

ምሳሌ ልስጥ ፦ ሁሉም ሰው የኃጢአት ዕዳ አለበት እናም ኢየሱስ ለሁሉም ሰው እዳቸውን ከከፈለ ለምን ሰዎች ባለማመናቸው እና በሌሎች ሌሎች ምክንያቶች ይቀጣሉ? ሰለሰዎች ሁሉ ኃጢአት ኢየሱስ ተቀጥቶ እዳቸውን ከከፈለ እግዚአብሔር መልሶ ሰዎችን ሰለኃጢአታቸው የሚቀጣ ከሆነ እግዚአብሔርን ኢፍትሐዊ አምላክ ያደርገዋል ።

እግዚአብሔር በ ደብል ጆፓርዲ (double Jeopardy) ይከሰሳል ማለት ነው!  ደብል ጆፓርዲ (double Jeopardy) ማለት – ሰለ ተመሳሳይ ጥፋት አንድን ሰው ሁለት ጊዜ የመቅጣት ተግባር ነው ። በተለይም በመጀመሪያው ችሎት በነጻ ከተለቀቀ በኋላ ሌላ ጊዜ መንገድ ላይ ጥፋተኛውን ሲያየው…. አንተ ያን ጊዜ ወንጀል የሰራኸው አይደል?  ና አሁን እስር ቤት ግባ እንደማለት ነው ። ልክ እንዲሁ ለሰዎች ሁሉ የሚያስፈልገውን እዳ ከከፈለ በኃላ ሰዎችን መልሶ መቅጣት ደብል ጆፓርዲ ( double Jeopardy) ነው ።

2,  እግዚአብሔር አቅዶ መፈፀም የማይችል ደካማ አምላክ ያደርገዋል ።

ማለትም እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው እንዲድን አቅድ ልጁን በመሰቀላይ አሳልፎ ሰጥቶ እያንዳንዱ ሰው አይድንም ማለት ምን ማለት ነው ። ይህ ከመፅሐፍ ቅዱሰ ጋር ሰሙሙ አይደለም ።

በመፅሐፍ ቅዱስ ውሰጥ የምናገኘው እግዚአብሔር ያቀደው ነገር የሚያደርግ ደግሞም ያቀደው ከመሆን የሚከለክለው አንድም ነገር እንደሌለ ነው ! በመፅሐፍ ቅዱስ ውሰጥ የእግዚአብሔር ባህሪ የተገለጠው በዚህ መልኩ ነው ።

– ኢዮብ 42፥2 (አዲሱ መ.ት) ““አንተ ሁሉን ማድረግ እንደምትችል፣ ዕቅድህም ከቶ እንደማይሰናከል ዐወቅሁ።”

– ሐዋርያት 4፥28 (አዲሱ መ.ት) “ይህም የሆነው የአንተ ክንድና ፈቃድ ጥንት የወሰኑት እንዲፈጸም ነው።”

– ኤፌሶን 1፥11 (አዲሱ መ.ት)  “ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል፤”

## ሊቋቋሙት የማይችሉት ፀጋ Irresistible Grace

Westminster Confession Chapter 10 - Of Effectual Calling ምዕራፍ 10 - እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሕይወት የወሰናቸው ሁሉ ፥ እነሱንም ብቻ ፣ እርሱ በወሰነውና ደሰ ባለው ወቅት በልዩ ጥሪው ለመጥራት መልካም ፈቃዱ ሆነ ።  ይህም ጥሪ በቃሉና በመንፈሱ መሳሪያነት ነው። በባሕርያቸ ከሚገኙበት ከኃጢአትና ከሞት በኢየሱሰ ክርሰቶሰ ወደ ፀጋና ወደ ድነት ጠራቸው ። የእግዚአብሔርን ነገር እንዲገነዘቡ አእምሮአቸውን ለመንፈሳዊና ለድነት ነገሮች አበራላቸው ። የድንጋዩን ልብ ወሰዶ የሰጋን ልብ ሰጣቸው ። ፈቃዳቸውን በማደስ ፥ በታላቅ ሀይሉ መልካሙን እንዲመርጡ አደረጋቸው ። በእርግጥም ወደጌታ ኢየሱሰ ክርሰቶሰ አቀረባቸው። ይህንንም ሁሉ ሲያደርግላቸው ፥ ተገደው ሳይሆን በራሳቸው ምርጫ በፀጋው ፈቃደኛ እንዲሆኑ በማድረግ ነው ።

– ሰፐርጅን እንዲህ ይላል: "ሰው ያለ ፈቃዱ አልዳነም ፣ ነገር ግን በመንፈሰ ቅዱሰ አሠራር ነው ፈቃደኛ የሆነውን ።

የዚህ አሰተምህሮ ዋናው  ትኩረት ለሚከተለው ጥያቄ የሚሰጠው መልሰ ነው ፦ አንዱ ሰው ለምን በወንጌልን ያምናል? ሌላው ደግሞ ለምን በወንጌል አያምንም ? አንድ ሰው ብልህ ሰለሆነ፣ የተሻለ የማመዛዘን ችሎታ ሰላለው ነው የወንጌልን መልእክት አሰፈላጊነት እንዲገነዘብ ያሰችለው ?   ወይሰ እግዚአብሔር በሚያድናቸው ሰዎች ሕይወት ውሰጥ ልዩ የሆነ ነገር ሰላደረገ ነው?

የሰውን ሁኔታ አስቀድመን ስንመለከት ለእግዚአብሔር ነገር ሙት የሆነ ፣ የእግዚአብሔርን ነገር መረዳት የማይችል እንደሆነ ገልፀን ነበር ። "እግዚአብሔርን ቢያውቁም እንኳ፣ እንደ አምላክነቱ አላከበሩትም፤ ምስጋናም አላቀረቡለትም፤ ነገር ግን ሐሳባቸው ፍሬ ቢስ ሆነ፤ የማያስተውል ልባቸው ጨለመ።" — ሮሜ 1፥21 (አዲሱ መ.ት) ። ታድያ ይህ ሰው እንዴት ከእዚህ የልብ ጨለማነት እራሱን ነፃ ሊያወጣ ይችላል ?

## –Regeneration

አንድ ሰው ከማመኑ አስቀድሞ በውስጡ ስራ ሊሰራ ይገባል ። ይህም መንፈስ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ የሚሰራ ስራ እንጂ በራሱ በሰውዬው የሚሰራ ስራ አይደለም ። እንዲሁም ፦ "በእውነት የሚመላለስ ግን ሥራው በእግዚአብሔር የተሠራ መሆኑ በግልጽ ይታይ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።"" — ዮሐንስ 3፥21 (አዲሱ መ.ት) ። ይህ ሰው አስቀድሞ በጨላ ያለ ፣ ደግሞም ወደብርሃን መምጣት ያቃተው ሰው ነበር ። ታዲያ ወደብርሃን እንዴት መጣ? ስራው በእግዚአብሔር ተሰርቶለት ።

ይህንን አስቀድሞ እንዲህ በማለት ገልፆአል ፦ "ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣ ወዴት እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው።"" — ዮሐንስ 3፥8 (አዲሱ መ.ት) ። በውስጣችን ምን እንኳን እንደተከናወነ ሳናውቅ ስራውን እግዚአብሔር ይሰራል ። ስራው ከተሰራ በኋላ ማን እንደሰራው ምን እንደተሰራ እናውቃለን ። ልክ ኤፌሶን ላይ ከሙታን ከክርሰቶስ አስነሳን እንደሚለው ። አንድ ሰው ከሙታን እንዴት እንደሚነሳ አስቦ አሰላስሎ አይደለም የሚነሳው ። ነገርግን ከሙታን ሲነሳ ማን እንዳነሳሳው እና ምን እንደነበር ይረዳል ። ልክ እንደዚሁ በ Regeneration ጊዜ የእኛ ተሳትፎ ምንም የለም ። ከእዚህ የተነሳ ወደ እምነት እንመጣለን ። ልክ እግዚአብሔር ለልዲያ እንዳደረገው ። ሐዋርያት 16 (አዲሱ መ.ት) [14] ከሚያዳምጡትም ሴቶች መካከል ልድያ የምትባል አንዲት ሴት ነበረች፤ እርሷም እግዚአብሔርን የምታመልክና ከትያጥሮን ከተማ የመጣች የቀይ ሐር ነጋዴ ነበረች። ጌታም፣ ጳውሎስ የሚናገረውን በማስተዋል ትሰማ ዘንድ፣ ልቧን ከፈተላት። [15] እርሷና ቤተ ሰዎቿ ከተጠመቁ በኋላም፣ "በጌታ ማመኔን በርግጥ ከተረዳችሁልኝ ወደ ቤቴ መጥታችሁ ጥቂት ተቀመጡ" በማለት አጥብቃ ለመነችን።

– እንደዚሁም በተመሳሳይ መንገድ በቲቶ ላይ እናገኛለን ፦ ቲቶ 3 (አዲሱ መ.ት)[3] ቀደም ሲል እኛ ራሳችን ማስተዋል የጐደለን፣ የማንታዘዝ፣ የተታለልን፣ ለተለያየ ምኞትና ምቾት ባሪያ ሆነን የተገዛን ነበርን፤ እየተጣላንና እርስ በርስ እየተጠላላን በክፋትና በምቀኝነት እንኖር ነበር። [4] ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ [5] ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤

አንድን ግለሰብ ንሰሐ እንዲገባና ወንጌልን እንዲያምን የመንፈስ ቅዱስን ሥራ እንጠቅሳለን። ማንም አስቀድሞ እግዚ አብሔር ካልሳበው በቀር ወደ ክርሰቶስ ሊመጣ እንደማይችል በቅዱሳት መጻሕፍት እንመለከታለን። ሙሉ በሙሉ የተበላሸን በመሆናችን እግዚ አብሔርን በራሳችን አንመርጥም ። ስለዚህ ወደ ክርሰቶስ የሚመጡት በመጀመሪያ በእሱ እንደሚሳቡ ግልጽ ነው ።

### – መንፈስ ቅዱ ስራውን በመረጣቸው ሰዎች ውሰጥ ስለሚሰራ ሰዎች የግድ ያምናሉ

ዮሐንስ 6 (አዲሱ መ.ት) ። [35] ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም። [36] ነገር ግን እንደ ነገርኋችሁ፣ አይታችሁኝም እንኳ አታምኑም። [37] አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔ የሚመጣውንም ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤

።

ለምሳሌ ሁለት አይነት ጥሪን እንመልከት ። የሰርግ ቤት ጥሪ ሲኖረን ከፈለግን እንሄዳለን ካልፈለግን እንቀራለን ። የፍርድቤት ጥሪ ከሆነ ግን ጥሪው በራሱ አንቀልቅሎ ነው የሚወስደው ። የእግዚአብሔርም ጥሪ ልክ እንደዚሁ ነው ። በእግዚአብሔር ከተጠራህ መቅረት አትችልም ። ይልቁኑም መምጣትህ አይቀርም ።

ከእነዚህ ጋር ተያይዞ እምነት የእግዚአብሔር ሰጦታ እንጂ የሰዎች የማገናዘብ ችሎታ ውጤት አይደለም ። ለምሳሌ ፦ ፊልጵስዩስ 1 (አዲሱ መ.ት) ²⁸ በማንኛውም መንገድ በተቃዋሚዎቻችሁ አትሸበሩ፤ ይህ እነርሱ እንደሚጠፉ፣ እናንተ ግን እንደምትድኑ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ምልክት ነው። ²⁹ በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ ተሰጥቶአችኋልና፤

– "የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ ስምዖን ጴጥሮስ፤ በአምላካችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኩል እንደ ተቀበልነው ዐይነት ክቡር እምነት ለተቀበሉት፤" — 2ኛ ጴጥሮስ 1፥1 (አዲሱ መ.ት) ።

### <u>አይገፌ የእግዚአብሔር ፀጋ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች</u>

ከሚነሱ ጥያቄዎች መካከል አንዱ ሐዋርያት ስራ 7:51 ላይ ያለው ነው ። ""እናንት ልባችሁና ጆሮአችሁ ያልተገረዘ፣ አንገተ ደንዳኖች ልክ እንደ አባቶቻችሁ መንፈስ ቅዱስን ሁል ጊዜ ትቃወማላችሁ።" ሐዋርያት 7፥51 (አዲሱ መ.ት) ። ከእዚህ በመነሳት የመንፈሰን ቅዱስን ጥሪ መቃወም እንደሚቻል መመልከት እንችላለን ይላሉ ።

1ኛ, በዚህ ክፍል መንፈስ ቅዱስን የተቃወሙት በእግዚአብሔር የተመረጡ መሆናቸውን ማስረጃ ማቅረብ የማይቻል በመሆኑ ተቃውሞውን ደካማ ያደርገዋል ።

2ኛ, በእግዚአብሔር የተመረጡ ናቸው ብንል እንኳን የወንጌል ስብከት ጥሪ በተደረገላቸው ጊዜ ሁሉ ያምናሉ ማለት ሳይሆን ። እግዚአብሔር እንዲድኑ በተወሰነበት ዕለት ይድናሉ ማለታችን ነው ። ካልቪኒስቶች ጸጋን መቋቋም አይቻልም ሲሉ፣ መንፈስ ቅዱስ አብ የመረጣቸውንና ክርስቶሰን የዋጃቸውን እሱ በወሰነው ጊዜ ከመጥራት፣ ከማደስ እና ከማዳን አይከለከልም ማለታቸው ነው።

## <u>የተረጋገጠ የድነት ዋሰትና</u>

በርካታ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ድነት ለዘለአለም የተጠበቀ መሆኑን በግልጽ የሚያብራሩ ቢሆንም በተወሰኑ የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባባት ላይ መሰረት በማድረግ ድነት ለዘለአለም የተጠበቀ መሆኑን ለማብራራት ሙከራ አደርጋለሁ ። ይህንን ለመረዳት አስቀድሞ የነበርንበትን ሁኔታ እንረዳ ከእዚያም አሁን ያለንበትን እንረዳ ። ከእዚያም ለወደፊቱ ምን እንሆናለን የሚለውን እንመለከታለን ። ለምሳሌ በኤፌሶን መፅሐፍ ምዕራፍ 2:1-10 ባለው ውስጥ ይህንን አይነት ቅደም ተከተል እንመለከታለን ። ከቁጥ 1-3 ምን ነበርን ? ከቁጥር 4-6 ምን አደረገን ? ከቁጥር 7-10 ያደረገንን ያደረገን ምን ሊያደርገን ነው ይለናል ።

ምን ነበርን? ሙታን ነበርን ። ምን አደረገን ? ከክርስቶስ ጋር ህያዋን አደረገን ። ህያዋን ከሆንን በኋላስ ዳግመኛ በሞት እንያዛለን ? መፅሐፍ ቅዱሳችን በፍፁም ነው መልሱ ። ይህንን በዮሐንስ ወንጌል 5:24 መመልከት እንችላለን ። ""እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚሰማ፣ በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።" — ዮሐንስ 5፥24 (አዲሱ መ.ት) ።

ይህንን የፍርድ ሀሳብ አስቀድሞ በምዕራፍ 3:16 ገልፆልን ነበር ። የማያምን ሰው አሁን ተፈርዶበታል ። ታድያ ያመነ ሰውስ ? ዳግመኛ ፍርድ ውስጥ አይገባም እያለን ነው ። የሮሜም መፅሐፍ ይህንን አይነት አገላለጽ ይጠቀማል ። ሮሜ 6 (አዲሱ መ.ት) [8] ከክርስቶስ ጋር ከሞትን፣ ከእርሱ ጋር እንደምንኖር እናምናለን። [9] ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶአልና፣ ዳግመኛ እንደማይሞት እናውቃለንና፤ ሞት ከእንግዲህ በእርሱ ላይ ጕልበት አይኖረውም።

## የቅዱሳንን ፅናት በየጴጥሮስ ሕይወት

በክርስቶስ ታምኖ በኢየሱስምድራዊ አገልግሎት ሁሉ ሲወዛወዝ እናያለን። ነገር ግን በመጨረሻ ጴጥሮስ ኢየሱስን ሲክደው እንመለከታለን ። በመቀጠልም በኢየሱስ ምልጃ እግዚአብሔርን ማገልገል መጀመሩን ማስተዋል ይቻላል ። ሉቃስ 22 (አዲሱ መ.ት) [31] ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “ስምዖን፣ ስምዖን ሆይ፤ እነሆ፣ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ [32] እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አበርታ።”  በቁጥር 31 ላይ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ የሚለውን Plural አድርጎ ሲገልፅ - በቁጥር 32 ላይ ደግሞ ኢየሱስ እምነትህ እንዳይጠፋ ስለአንተ አማለድሁ በማለት singular ያደርገዋል ።

ሰይጣን እንደ ስንዴ አብዝቶ ሊያበጥራቸው ወደደ ብሎ plural አድርጎ ሲገልፅ በይሁዳ እና ጴጥሮስን መሆኑ ግልጽ ነው ። አስቀድሞ በቁጥር 22 ስለይሁዳ ተናግሮ ነበር “ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው እጅ በማእድ ከእኔ ጋር ናት።” ሉቃስ 22፥21 (አዲሱ መ.ት) ። ጴጥሮስ በእግዚአብሔር የተመረጠ በመሆኑ እምነቱ አልጠፋም ። በኢየሱስ ምልጃ እንደገና ተመልሷል ። ይሁዳ ግን የጥፋት ልጅ ስለነበር አልተመለሰም ።  የእግዚአብሔር የሆኑቱ እንዳይጠፋ የክርስቶስ ምልጃ ዋስትና ነው ። በክርስቶስ ምልጃም የምናምንበት አንዱ ምክንያት ለዘለአለም ዋስትናችን ነው ። ዮሐንስ 10 (አዲሱ መ.ት)[28] እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም። [29] እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፤ ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው አይችልም።

## 2ኛ ጴጥ 3:8-9

[8] ወዳጆች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፣ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን መሆኑን ይህን አንድ ነገር አትርሱ።[9] እንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው ጌታ የተሰፋ ቃሉን ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ፣ ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሣል።

### የተሰፋ ቃሉን ለመፈፀም

በእዚህ ውስጥ የተሰጠ ተሰፋ አለ ይህም ደግሞ መፈፀሙ የማይቀር ነው ይለናል ።  ምንድነው ተሰፋው ? ይህንን የተሰፋ ቃል 4 ቁጥር ወረድ ስንል የምናገኝ ይሆናል ።  “ደግሞም የእግዚአብሔርን ቀን እየተጠባበቃችሁ መምጫውን ልታፋጥኑ ይገባል። በዚያን ቀን ሰማያት በእሳት ተቃጥለው ይጠፋሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በታላቅ ትኵሳት ይቀልጣል።” “እኛ ግን ጽድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተሰፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን።” — 2ኛ ጴጥሮስ 3፥13 (አዲሱ መ.ት) ። ስለዚህ ይህ ተሰፋ መፈፀሙ ስለማይቀር ሁሉ ወደ ንሰሃ **እንዲበቃ** እርሱ **ይታገሣል**  ይለናል ።

እዚህ ጋር መጠየቅ ያለብን ጥያቄ ሁሉ ወደ ንስሃ ይበቃል ?

እዚህ ጋር እርግጠኛ መሆን ያለብን ሁሉ ለንሰሃ ብቁ ይሆናሉ ። ግን ሁሉ ሲል እያንዳንዱ ማለቱ ነው ? ይህ ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው ። ምክንያቱም ሁሉ ለንሰሐ የሚበቁ ከሆነ ሲኦል የሚገባ የለም ማለት ነው ይህ ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው ። ለምሳሌ ፦ ዳንኤል 12 (አዲሱ መ.ት) [1] "በዚያን ዘመን ስለ ሕዝብህ የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል። መንግሥታት ከተመሠረቱበት ጊዜ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል። ነገር ግን በዚያን ጊዜ ስማቸው በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ ይድናሉ። [2] በምድር ዐፈር ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ አንዳንዶቹ ለዘላለም ሕይወት፣ ሌሎቹም ለውርደትና ለዘላለም ጉስቍልና ይነሣሉ።

ደግሞም በእዚሁ መፅሐፍ አውድ መሰረት ይህንን መመልከት እንችላለን ። እግዚአብሔር የሚፈረድባቸው ሰዎች አሉ እነርሱ ላይ ይፈርዳል ብሏል ። ታድያ ሁሉ ብሎ የሚጠራው እነማንን ነው በአዳኛ በክርሰቶሰ ያመኑ ማለቱ ነው ።

የእዚህ መፅሐፍ ሀሳብ ከይሁዳ መልዕክት ጋር ጎን ለጎ ማየት የምንችለው መፅሐፍ ነው ። የይሁዳ መልዕክትም ሀሰተኞችን እንደሚቀጣ የእርሱ የሆኑትን ደግሞ እሰከመጨረሻው እንደሚያፀና ይነግረናል ። ይሁዳ 1 (አዲሱ መ.ት) ። [24] እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችለው፣ [25] እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው አምላክ በጌታችን በኢየሱሰ ክርሰቶሰ በኩል ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እሰከ ዘላለምም ድረሰ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና ሥልጣን ይሁን፤ አሜን ።

## <u>1ኛ ተሰሎንቄ 5:1-10</u>

– ቁጥር 10 "ብንነቃም ሆነ ብናንቀላፋ ከእርሱ ጋር በሕይወት እንድንኖር እርሱ ሰለ እኛ ሞተ።"

ይህ አገላለጽ በየትኛውም አይነት ሁኔታ ውሰጥ ብንሆንም ክርሰቶሰ አይተወንም ። ዋጋ የከፈለልን ከእርሱ ጋር በህይወት እንድንኖር ነው የሞተው ።

ከእዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጥያቄ መንቃት እና ማንቀላፋት መሞት እና ከሞት መነሳት ነው በምዕራፍ 4 ገለፃ ይላሉ ። "ወንድሞች ሆይ፤ አንቀላፍተው ስላሉ ሰዎች ሳታውቁ እንድትቀሩ አንፈልግም፤ ደግሞም ተሰፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ሰዎች እንድታዝኑ አንሻም።" — 1ኛ ተሰሎንቄ 4፥13 (አዲሱ መ.ት) ።

**κοιμάω (ኮኢማኦ)** የሚል ሲሆን ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውሰጥ 18 ጊዜ ተጠቅሷል ። አብዛኛው ቦታ ላይ በቀጥታ ከሞት ጋር ተያይዞ ነው የተጠቀሰው ።

በምዕራፍ 5 ላይ ግን የሚጠቀመው ቃል በምዕራፍ 5 ከገለፀው ጋር ተመሳሳይ አይደለም ። በምዕራፍ 5 የሚጠቀመው ቃል **καθεύδω (ካእቲውዶኦ)** የሚል ነው ። ይህም በአዲስ ኪዳናችን ለ22 ጊዜ ነው የተጠቀሰው ። በጣም የሚገርመው አንድም ቦታ ከሞት ጋር ተያይዞ አልተጠቀሰም ። ሰለዚህ ሰለሞት እያወራ ሊሆን አይችልም ። ሰለሞት እያወራ ከሆነ ለምን የተለያዩ ቃላቶችን መጠቀም አሰፈለገ ?

ምዕራፍ 5 ላይ ያለው ማንቀላፋት ሞትን እንደማይወክል በምዕራፍ 5:6 መመልከት እንችላለን ። **<u>"እንግዲህ</u>**

**እንንቃ !** እንንቃ የሚለው ቃል ሞትን የሚወክል ከሆነ ተደራስያኑ ሞተው ነበር ወይ ? ጳውሎስ እራሱን አካቶ ነው የሚያወራው ጳውሎስስ ሞቶ ነበር ወይ ? ደግሞስ ሞተው ቢሆን እንኳ እንቃ ብለው ነው እንዴ የሚነቁት ? ስለዚህ ስለሞት እያዋራ አይደለም ። ከእዛህ ይልቅ ማንቀላፋት በጨለማ መመላለስን ሲወክል ፣ መንቀት ደግሞ በብርሃን መመላለስን ይወክላል ።

## ከሰነ እምክንዮ አንፃር

– የድነታችን መሰረት የእግዚአብሔር ፍቅር ነው ! የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው ! ስለዚህ ድነት ዘላለማዊ ነው ! ሰው ከዳነ በኋላ ሊጠፋ ይችላል ማለት የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ አይደለም ማለት ነው !

– የተቀበልነው ዘላለማዊ ህይወት የሚጠፋ ከሆነ ዘላለም ለሚለው ቃል ሌላ ትርጉም ልንፈልግለት ያስፈልጋል ። በእኔ ምልከታ ፅድቅ በእምነት ብቻ የሚለውን ተቀብለን የቅዱሳንን ፅናትን የማንቀበል ከሆነ Contradiction ውስጥ ገብተናል ። ፅድቅ በእምነት ብቻ ስንል በማመናችን ብቻ ያለእኛ ተሳትፎ ወደ እግዚአብሔር ቀርበናል በመቅረብም እንቀጥላለን ማለት ነው ። ይህንን ካመንን በኋላ በስራችን ድነትን እናጣለን ደግሞም ድነታችንን በስራ እናስቀጥላለን ብሎ ማለት ተቃርኖ ውስጥ ያስገባናል ።

በህይወት መዝገብ ላይ ስራችን ሳይሆን ስማችን ተፅፏል ሰማችን በህይወት መዝገብ ላይ እንዲፃፍ ስራችን በክርስቶስ ተሰርቷል ።

## ማጠቃለያ

የእግዚአብሔር ወንጌል ከእግዚአብሔር ለሰዎች የተላከ መልእክት ስለሆነ ይህ መልእክት በሰዎች ፈንታ የእግዚአብሔርን ሥራ ማወጅ ነው።   ድህነት ከእግዚአብሔር በእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ነው !!

ማለትም: ከእግዚአብሔር :- መነሻ ምክንያት ሲሆን ከእርሱ መልካም ተነሳሽነት መሆኑን የሚገልጽ ነው ። “ነገር ግን በምሕረቱ ባለጠጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፣” — ኤፌሶን 2፥4 (አዲሱ መ.ት)

በእግዚአብሔር – ይህ ደግሞ መንገድ ነው ። ማለትም የእግዚአብሔር ምህረት የሚገለጥበት መንገድ ። “በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣ ቤዛችንም ሆኖአል።” 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥30 (አዲሱ መ.ት)

ለእግዚአብሔር – ይህ ደግሞ አላማን የሚገልጽ ነው ። ማለትም ደሞዝ ለስራ ነው ። እኛ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ስጦታ እንጂ ደሞዝ አይደለም ። “ይኸውም በሚመጣው ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ በቸርነቱ የገለጠልንን ወደር የሌለውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ነው፤” ኤፌሶን 2፥7 (አዲሱ መ.ት)

እግዚአብሔር እኛ ሳንፈጠር የነበረ ያለ እኛ መኖር የሚችል አምላክ ነው ። እኛ ግን ያለ እርሱ ሕይወት የሌለን ፍጥረት ነን። በራሳችን ኃጢአት ምክንያት ከእርሱ ጋር ተጣልተን ከእቅፉ በወጣን ጊዜ ያለ እኛ መኖር እየቻለ ግን ለኛ መኖር ብሎ መታረቅን ከእኛ ይልቅ ፈለገ።  በግድ "ካልታረቅን!" ብሎ ልጁን አማላጅ አድርጎ ላከልን። ያለ እርሱ መኖር የማንችለው እኛ ግን፣ ባንታረቅ የምንጠፋው እኛ  "እንታረቅ" ብሎ የለመነን ግን እሱ።  ከዳንን መንግስተ ሰማይ የምንገባው እኛ  ልጁን መስዋዕት ያደረገው እሱ ። መትረፋችን አንዳች ላይጨምርለት መሞታችንም አንዳች ላይቀንስበት ግን ስለወደደን ብቻ የውድ ልጁን ደም አፍስሶ ታረቀን።

**በ ተካልኝ ኃ/ሚካኤል**